# በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

# የ40/60 እና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች

# የምዝገባ ማስፈጸሚያ ሰነድ

# (የመጀመሪያ ረቂቅ)

**በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣**

**በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣**

**በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና**

**በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**

**በጋራ የተዘጋጀ**

ሰኔ 2005 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ፣</u>

## ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------------------- | 1 |
| 2. | አጭር ርዕስ ------------------------------------------------------------------------------------------- | 2 |
| 3. | ትርጓሜ ------------------------------------------------------------------------------------------- | 2 |
| 4. | የማስፈጸሚያ ሰነዱ ዓላማ ------------------------------------------------------------------------- | 2 |
| 5. | የማስፈጸሚያ ሰነዱ ጠቀሜታ ------------------------------------------------------------------------- | 3 |
| 6. | መርሆዎች ------------------------------------------------------------------------------------------- | 3 |
| 7. | ዝርዝር አፈጻጸም ------------------------------------------------------------------------------------ | 3 |
| 7.1. | የ40/60 ፕሮግራም ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ | |
| 7.1.1. | የምዝገባ ቅጽና ቁጠባ ውል አሞላል ሂደት ------------------------------------------------------ | 3 |
| 7.1.2. | የቁጠባ ስርዓት ------------------------------------------------------------------------------------ | 4 |
| 7.1.3. | የመኖሪያ ቤቶች ስፋት፣ ጠቅላላ ዋጋ እና ቅድመ ቁጠባ --------------------------------------------- | 5 |
| 7.1.4. | ተግባርና ኃላፊነቶች ------------------------------------------------------------------------------ | 5 |
| 7.1.5. | ልዩ ልዩ ጉዳዮች ------------------------------------------------------------------------------------ | 8 |
| 7.2. | የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ---------------------------------- | 9 |
| 7.2.1. | የምዝገባ ቅጽና ውል አሞላል ሂደት --------------------------------------------------------------- | 9 |
| 7.2.2. | የቁጠባ ስርዓት | 10 |
| 7.2.3. | የመኖሪያ ቤቶች ስፋት፣ ጠቅላላ ዋጋ እና ቅድመ ቁጠባ | |
| 7.2.4. | ተግባርና ኃላፊነቶች ------------------------------------------------------------------------------ | 11 |
| 7.2.5. | ልዩ ልዩ ጉዳዮች ------------------------------------------------------------------------------------ | 15 |
| 8. | የማስፈጸሚያ ሰነዱን ስለማሻሻል ------------------------------------------------------------------- | 16 |
| 9. | የማስፈጸሚያ ሰነዱ ስለሚጸናበት ሁኔታ --------------------------------------------------------- | 16 |
| | አባሪ አንድ ------------------------------------------------------------------------------------------- | 17 |
| | አባሪ ሁለት ------------------------------------------------------------------------------------------- | 19 |

## 1. መግቢያ

በአዲስ አበባና በዋና ዋና ከተሞች እያደገ የመጣውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት መንግስት የቤት ልማት ፖሊሲን ቀርጾ በፖሊሲውም በከተሞች በተለያዩ የቤት ልማት አቅርቦት ስልቶች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ልማትን በማፋጠን የነዋሪውን ህብረተሰብ የቤት ችግር ከመፍታት ጎን ለጎን ከተሞችን በማሳደግ ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞች አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ማድረግ ነው፡፡

በዚህ ሂደት ባለፉት ዓመታት አንዱ የቤት ልማት አቅርቦት አማራጭ በሆነው በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም (20/80) በክልሎችና በአዲስ አበባ ከ200 ሺህ በላይ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ከ60 በመቶ በላይ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ የተቻለ ቢሆንም ከቤት ፈላጊው ነዋሪ ህብረተሰብ ቁጥርና አቅም ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ መንግስት ከዚህ ፕሮግራም በተጨማሪ የአነስተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች(10/90)፣ መካከለኛ ገቢ ላላቸው 20/80 ነባርና አዲስ፣ የቁጠባ ቤቶች ልማት(40/60) እና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቤት ልማት ፕሮግራሞችን ነድፎ በአዲስ አበባ ከተማ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በክልሎችም ተጨባጭ የቤት ፍላጎት ተጠንቶ የሚጀመር ይሆናል፡፡

በነዚህ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የሚሆኑ ነዋሪዎችን ለመለየት ነበሩን የኮንዶምኒዬም ምዝገባ አጣርቶ ዳግም ከመመዝገብ በተጨማሪ አዲስ በተቀረጹት የቤት ልማት አማራጮች ተጠቃሚ የሚሆኑትን ለመለየትና የፋይናንስ ዝግጅት እንዲያደርጉ የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ወጥቶ ምዝገባው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁና በቀጣይ የሚደራጁ እንዲሁም የ40/60 ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

ሆኖም ግን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ቆጥበው በቤት ልማት ፕግራሙ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የቤት ባለቤት እንዲሆኑና ከእናት ሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ከማጥበቅ ጎን ለጎን ለኢኮኖሚው አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ግልጽ የምዝገባ፣ የአደረጃጀትና የቁጠባ ስርዓቱን የሚያሳይ ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ የባለድርሻ አካላትን ሰፊና የተቀናጀ ተሳትፎ የሚፈልግ በመሆኑ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውን በ40/60 እና በመኖ/ህ/ስ/ማ ቤት ልማት ፕሮግራሞች ለመጠቀም ሲያመለክቱ

የምዝገባና ቁጠባ አሰራር ስርዓቱን ወጥነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት በተሞላ መልኩ በቅንጅትና በመናበብ ለማካሄድ ሲባል ይህን ዝርዝር የምዝገባ የጋራ ማስፈጸሚያ ሰነድ በጋራ አውጥተዋል።

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ ማስፈጸሚያ ሰነድ "በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የ40/60 እና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፈጸሚያ ሰነድ ቁጥር 01/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. ትርጓሜ

1) **"ዲያስፖራ"** ማለት በውጭ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ማለት ነው።
2) **"ሀዋላ"** ማለት በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የማዘዋወር ዘዴ ነው።
3) **"ዲፕሎማቲክ ፓውች"** ማለት የተቀባዩን አገር ሕግ የማይጻረርና በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚሲዮን ወይም ቆንስላ ኦፌሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ማለት ነው፣
4) **"ሚሲዮን"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ማለት ነው፣
5) **"ነባር ማህበራት"** ማለት በ1996 እና በ1997 ዓ.ም. በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያውያን ተቋቁሞ እስካሁን ድረስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ ያልተረከበ ህብረት ስራ ማህበር ነው፡
6) **"አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት የመ/ቤ/ህ/ስ/ማህበራት መመሪያ ጸድቆ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚቋቋም የቤት ስራ ማህበር ማለት ነው።
7) **"ተወካይ"** ማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በኢትዮጵያ ሰነዶች ማረጋገጫ ባለስልጣን በኩል በተረጋገጠ ህጋዊ ውክልና በአባላቱ የተሰጠው ሰው ማለት ነው፣
8) **"ንግድ ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማለት ነው፣

## 4. የማስፈጸሚያ ሰነዱ ዓላማ

1) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ከምዝገባ ጀምሮ የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአሰራር ሂደት ግልጽ ለማድረግ፣

በምዝገባ ሂደት የሚሳተፉ አካላትና ተቋማት በመቀናጀትና በመናበብ እንዲሰሩ ግልጽ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለይተው እንዲያስፈጽሙ ለማድረግ፣

5. **የማስፈጸሚያ ሰነዱ ጠቀሜታ**

ይህ ልዩ ማስፈጸሚያ ሰነድ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በ40/60 እና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች በመመዝገብ ሂደት የባለድርሻ አካላት ግልጽ አረዳድ ኖሯቸው እንዲተገብሩና ክፍተት እንዳይፈጠር ይረዳል፣

6. **መርሆዎች**

   1) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚካሄዱ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለሀገራቸው ልማት አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡
   2) ግልጽ እና ፈጣን የምዝገባ፣ የቁጠባና የአደረጃጀት ስርዓት በመከተል መረጃዎች ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
   3) ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ባቀናጀ መልኩ ለአንድ ዓላማ በጥራትና በፍጥነት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለመደገፍ የጋራ ጥረት ይደረጋል፡፡

7. **ዝርዝር አፈጻጸም**

## 7.1. የ40/60 ፕሮግራም ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ

### 7.1.1. የምዝገባና ቅጽና ቁጠባ ውል አሞላል ሂደት

በ40/60 የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 21/2005 የተቀመጡት የምዝገባና የቁጠባ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣

ሀ. በውጭ ሀገር የሚኖሩ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባ መስፈርቱን አሟልተው 40 ከመቶና ከዚያ በላይ በአንድ ጊዜ የሚቆጥቡ ከሆነ የምዝገባ ቅጹንና የቁጠባ ውሉን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በየኢምባሲያቸውና ቆንሲላ ጽ/ቤታቸው አማካኝነት እንዲላክላቸው በማድረግ ሙሉ በሙሉ ሞልተውና ፈርመው እንዲልኩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም የኤምባሲዎች ማህተም እንዳለው ተረጋግጦ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ይደረጋል፣

ለ. ከ40 በመቶ በታችና በየወሩ ቁጠባ የሚያደርጉ ከሆነ የምዝገባ ቅጹንና የቁጠባ ውሉን በራሳቸው ወይም በህጋዊ ተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲሞሉና የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፍቱ ይደረጋል፣

ሐ. በአካል የማይገኙትና የቁጠባ ውሉን ፈርመው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት የሚልኩትን በተመለከተ የቁጠባ ውሉን ቀሪ ድርሻ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደደረሰው የሚፈርም ሲሆን ኦርጂናል ውሉ ሲደርስ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የቁጠባ

ሂሳቡ የሚከፈትበት ሁኔታ ይመቻቻል፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኦሪጂናል ውሉንና የምዝገባ ቅጹን በማስሞላት ለባንኩ አስቀድሞ እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርበታል፣

መ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የ40/60 ቤት ፈላጊዎች የቁጠባ ውል ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተረክቦ በውጭ ሀገር በሚሲዮኖችና ቆንሲላ ጽ/ቤቶች አማካኝነት በማስፈረም ኦሪጅናሉን እንዲያቀርብ ይደረጋል፣

ሠ. በውጭ ሀገር የሚኖሩ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባና የቁጠባ ሂሳብ የመክፈት ሂደቱን ለማስፈጸም ወቅታዊ የፓስፖርት ኮፒ፣ የኢትዮጵያ ትዉልድ መታወቂያ ካርድ ኮፒ፣ የሚኖሩበትን ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ ከውሉና የምዝገባ ቅጹ ጋር ሁለት ፎቶ ግራፍ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፣

### 7.1.2. የቁጠባ ስርዓት

ሀ. 40 ከመቶና ከዚያ በላይ በአንድ ጊዜ የሚቆጥቡ ቁጠባውን በንግድ ባንክ በተከፈተዉ አካዉንት በመላክ የመላኪያ ደረሰኝ ኮፒ በኢምባሲያቸው አማካኝነት መላክ ይኖርበታል፣ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር እና በንግድ ባንክ አማካኝነት ከኤምባሲ ቢላከዉ ዝርዝር በመነሳት ወደ እያንዳንዳቸው የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፣

ለ ከ40 ከመቶ በታችና በየወሩ ለሚቆጥቡ ተመዝጋቢዎች በአካል ወይም በወኪላቸው አማካኝነት በተከፈው ሂሳብ በባንክ፣ በገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ወይም በጥሬ ገንዘብ በኢተዮጵያ ንግድ ባንክ ማስገባት ይችላሉ፤

ሐ. በሀገር ውስጥ በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን (ተመላሽ ዲያስፖራ) በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ተረጋግጦ ሲቀርብ ሊመዘገቡ ይችላሉ፣ የሚቆጥቡበት በብር ይሆናል፣

መ. ከዚህ በፊት በዲያስፖራ አካውንት ስም የተከፈተ ሂሳብ ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ቁጠባ ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፣

ሠ. ቁጠባ የሚደረገው ለመመዝገብ የፈለጉትን የቤት አይነትና የቁጠባ መጠን ከውጭ ምንዛሬ ወደ ኢትዮጵያ ብር ተቀይሮ በማንኛውም ኢትዮጵያ በምትገበያይባቸው የውጭ ምንዛሬ (በዶላር ዩሮና ፓዉንድ ስተርሊንግ) ነው፡፡

ረ. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ምንዛሬ የተላከውን ገንዘብ ወደ ብር በመቀየር የተከፈተው ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል፣ በውጭ ምንዛሬ የነበረው ወደ ብር ተቀይሮ ቁጠባ ይደረጋል፡፡

### 7.1.3. የመኖሪያ ቤቶች ስፋት፣ ጠቅላላ ዋጋ እና ቅድመ ቁጠባ

- ባለ 1 መኝታ ስፋቱ 55 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋ ብር 162,645 ሲሆን 40 ከመቶው ብር 65,058 ሲሆን ዝቅተኛው ወርሃዊ ቁጠባ ደግሞ ብር 1,033 በኢትዮጵያ ብር ይሆናል፣
- ባለ 2 መኝታ ስፋቱ 75 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋ ብር 250,000 ሲሆን 40 ከመቶው ብር 100,000 ሲሆን ዝቅተኛው ወርሃዊ ቁጠባ ደግሞ ብር 1,575 በኢትዮጵያ ብር ይሆናል፣
- ባለ 3 መኝታ ስፋቱ 100 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋ ብር 386,400 ሲሆን 40 ከመቶው ብር 154,560 ሲሆን ዝቅተኛው ወርሃዊ ቁጠባ ደግሞ ብር 2,453 በኢትዮጵያ ብር ይሆናል፣
- ከላይ የተጠቀሱት ዋጋዎች የሚያገለግሉት ለምዝገባና ቁጠባ ለማድረግ እንጂ የቤቶች ትክክለኛ የማስተላለፊያ ዋጋ የሚወሰነው ግንባታቸው ተጠናቆ በወቅቱ በሚወጣው ዋጋ መሰረት ይሆናል፣
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት የቁጠባ ሂደቱን ድጋፍ ማድረግ የሚቻለው አነስተኛው የቁጠባ መጠን 40 ከመቶ ሲደርስ ይሆናል፣

### 7.1.4. ተግባርና ኃላፊነቶች

#### 7.1.4.1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ሀ. በ40/60 ቤት ፈላጊነት ለሚመዘገቡ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ምዝገባውና ቁጠባውን የተቀላጠፈ ለማድረግ በምዝገባ፣ በቁጠባና በአደረጃጀት የሚሳተፉ አካላትና ተቋማትን የጋራ ስምምነት ዕቅድ በማዘጋጀት ስለ አፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ለ. ለ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚያስፈልገው መሬት ዝግጅት ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመጣመር መዘጋጀቱን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ሐ. ከመሬት ዝግጅቱ ጎን ለጎን የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት አቅርቦት በተቀናጀ አግባብ እየቀረበ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

መ. ለ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚገነቡ ቤቶች ስታንዳርድ ዲዛይን በማዘጋጀት እንዲሁም በራሳቸው ዲዛይን የሚገነቡ ካሉ ዲዛይኖችን የማጽደቅ ስራ ያከናውናል፣

ረ. በመንግስት የተደረጉና በቀጣይ ሊደረጉ የታሰቡ ሌሎች ድጋፎች በጸደቀው የቤት አቅርቦት ስትራቴጂ መሰረት ስለመሆኑ ይከታተላል፣

7.1.4.2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

1) **የሚሲዮኖች አጠቃላይ የስራ ድርሻ**

ሀ) በ40/60 መመዝገብ ለሚፈልጉ ቤት ፈላጊዎች ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ በሚሲዮኑ እንዲሁም ለሚወክሉባቸው አገሮች/ከተሞች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፣

ለ) የ40/60 ቁጠባ ቤት ልማት ፕሮግራም መመሪያው ላይ የተቀመጠው የምዝገባ ቀናት፣ የምዝገባ ቦታና ተመዝጋቢዎች የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እንዲያሟሉ በግልጽ የማስገንዘብ ስራ መስራት፣

ሐ) በ40/60 ቁጠባ ቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች እንዲሞሉ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተላኩ ቅጾችን በበቂ ሁኔታ በማዘጋጀት ማስሞላት፣

መ) በ40/60 ቁጠባ ቤት ልማት ፕሮግራም የተመዘገቡትን እንዲሁም የተሞሉ ቅጾችንና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን በጥንቃቄ በማደራጀት በዲፕሎማቲክ ፓውች በወቅቱ ለውጭ ጉዳይ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲደርስ ማድረግ፣

ሠ) ስለ 40/60 ፕሮግራም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የሚላኩትን የተለያዩ ሰነዶች፣ ቅጾችና ውሎች በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣

ረ) ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች እንዲሁም ማብራሪያ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ካጋጠሙ በወቅቱ ለዋናው መ/ቤት ማቅረብ፣

ሰ) የ40/60 ቁጠባ ቤት ልማት ፕሮግራም ምዝገባ በጸደቀው መመሪያ መሰረት ብቻ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

2) **በ40/60 ምዝገባ ፕሮግራም የሚሲዮኖች የስራ ድርሻ**

ሀ) ይህ ምዝገባ የሚካሄደው በዋናነት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ቢሆንም በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ በሚሲዮኖች በኩል እንዲሆን በመፍቀዱ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ምዝገባ በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዲፈጸም ማድረግ፣

ለ) በተላከላቸው የምዝገባ ቅጽ መሰረትና ከባንኩ ጋር የውል ስምምነት ቅጽ በተመዝጋቢው ተፈርሞ በዲፕሎማቲክ ፓውች ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲደርስ ማድረግ፣

ሐ) ከምዝገባ ቅጾችና ውል ሰነድ በተጨማሪ እያንዳንዱ ተመዝጋቢ የስም ዝርዝር እንዲሁም ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ አብሮ መላክ፣

መ) በምዝገባው መሰረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚላክለትን የቁጠባ ደብተር ለተመዝጋቢዎች በማድረስ በተከፈተላቸው የቁጠባ ሂሳብ ገንዘብ እንዲልኩ ማሳወቅ፣

3) **በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጄኔራል የስራ ድርሻ**

ሀ) ከሚሲዮኖች ጋር በቅርበት በመገናኘት አስፈላጊ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ቅጾች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚላኩ ውሎችን በወቅቱ ለሚሲዮኖች መላክ፤

ለ) ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር በወቅቱ ለሚሲዮኖች እንዲደርሱ ማድረግ፣

ሐ) ከሚሲዮኖች የሚላኩ የተሞሉ ቅጾችንና መረጃዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደትና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማድረስና ስለጉዳዩ ክትትል ማድረግ፣

መ) ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚሲዮኖች በተላከው መረጃ መሰረት በባንኩ የተፈረመ የውል ሰነድ ኮፒ እንዲሁም የተዘጋጀ በተመዘገበው ስም የተከፈተ የተሟላ የቁጠባ ደብተር ተቀብሎ ለሚሲዮኖች መላክ፣

ሠ) ከሚሲዮኖች፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት የሚደረጉ ግንኙነቶችን በተመለከተ መከታተልና መረጃ መያዝ፣

### 7.1.4.3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ሀ. በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በ40/60 የቁጠባ ፕሮግራም ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች የሚያስፈልግ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ይሰራል፤

ለ. በ40/60 ቤት ፈላጊዎች ለመመዝገብ ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች የቁጠባ ውል እና ሌሎች ሰነዶችን በማዘጋጀት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እንዲደርሳቸውና ፈርመው እንዲልኩ ያደርጋል፤

### 7.1.4.4. የአዲስ አበባ አስተዳደር ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ የሚያስፈልገውን ሶፍትዌር በማልማትና አጠቃላይ የቴክኖሎጂ አጠቃቀሙን በመምራት ይሠራል፣

### 7.1.5. ልዩ ልዩ ጉዳዮች

አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በ40/60 ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በሚደረግበት ወቅት ትኩረት አድርገው የሚመለከቷቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ይሆናሉ፣

1) **የምዝገባ ጊዜ**

የ40/60 ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ጊዜ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መጠናቀቅ ይኖርበታል። ሆኖም በቦታ እርቀትና በመረጃ እጥረት ምክንያት በወቅቱ ያልደረሱ መረጃዎች ካሉ በንግድ ባንክ ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፣

2) **የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ**

ሀ) የ40/60 ፕሮግራም ተጠቃሚ ከሆኑ የሂሳብ እንቅስቃሴው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በሚፈርሙት የቁጠባና የብድር ውል መሰረት ይሆናል፣

3) **የግንባታ ክትትልን በተመለከተ**

ሀ) በ40/60 ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክቱ ቤት ፈላጊዎች ህጋዊ ውክልና በሰጡት አካል በኩል ሊሆን ይችላል፣

ሐ) በመንግስት ድጋፍ በቤቶች ልማት ኢንተርፕራዝ አማካኝነት ቤቱ እንዲገነባላቸው የሚፈልጉ ከሆነ መንግስት አማካሪ በመቅጠር የግንባታ ክትትል ሊያደርግ ይችላል፣

4) **ቤት ርክክብና ቅድሚያ አወሳሰን**

ሀ) በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ቤት ፈላጊ ሆነው ተመዝግበው የቤቱን ዋጋ 100 የቆጠቡ በዋናው መመሪያ መሰረት ቅድሚያ ያገኛሉ፣

ለ) በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የተገነቡ ቤቶች በቁጠባና ብድር ውሉ በተሞላው ውል መሰረት የተጠናቀቀውን ቤት በራሳቸው ወይም በወኪላቸው አማካኝነት እንዲረከቡ ይደረጋል፣

5) **ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ**

ሀ) በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ቤት ፈላጊነት የተመዘገበ ማንኛውም ተመዝጋቢ በተመዘገበበት ፕሮግራም በፈቃደኝነት ከፕሮግራሙ ለመውጣት ከፈለገ ወይም የሚጠበቅበትን ቁጠባ የማይቆጥብ ከሆነ ከምዝገባው ተሰርዞ የቆጠበውን ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር እና በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት ወለዱ ታስቦ ይመለስለታል፣

ለ) ተመዝጋቢው የምዝገባ መመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እንደሆነ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ በህግ ሊጠየቅ ይችላል፣

6) **ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ**

ሀ) ከ40/60 ቁጠባ ፕሮግራም ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነ ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማህበር የሚመለሰው ገንዘብ በወቅቱ የኢትዮጵያ ገንዘብ ሆኖ በቁጠባ ውሉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚያገኘውን የወለድ ጥቅም በመጨመር ነው፡፡

7) **ክልከላ**

ሀ) በ40/60 የቁጠባ ቤቶች ፕሮግራም የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 21/2005፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚመለከት ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ መመዝግብም ሆነ እንዲመዘገብ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ለ) በመመሪያው የተቀመጡ ክልከላዎች በሙሉ በዚህ ማስፈጸሚያ ሠነድ ተፈጻሚነት አላቸው፣

8) **ቅጣት**

የ40/60 የቁጠባ ቤቶች ፕሮግራም የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 21/2005 የተቀመጡትን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ፣ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ እንደሆነ አግባብ ባለው በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

## 7.2. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ

### 7.2.1. የምዝገባና ቅጽና ቁጠባ ውል አሞላል ሂደት

ሀ. አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ ለመመዝገብ የሚችሉት ሁሉም የማህበሩ አባላት በመረጡት የቤት አይነት መጠን ከ50 በመቶ እስከ 100 በመቶ ቁጠባቸውን ማሟላት ሲችሉ ብቻ ነው፣

ለ.. ከተጠቀሰው ጊዜ በፊትም ሆነ በኃላ ለመመዝገብ ማናቸውም የህብረት ስራ ማህበራት ኃላፊነት የማህበሩ ይሆናል፣

ሐ ማህበራት እንደተቋቋሙ የሚቆጠረው በመረጡት የቤት አይነት መጠን ቢያንስ 50 በመቶ ቆጥበው ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

መ. ሁሉም የህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው መጠሪያ ሲኖራቸው በመጠሪያ ማህበራት ስር ያሉ አባላት በሙሉ የሚቀርብላቸውን ቅጽ በራሳቸው ወይም በወኪላቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ መሙላት ይገባቸዋል፣

ሠ. የህብረት ስራ ማህበራት አባላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣

ረ የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸውን ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ወይም በክልል አስተዳደሮች የሚመለከተው አካል ሲያጸድቀው ተግባራዊ ይሆናል፣

ሰ. ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በክልል ከተሞች በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በትውልድ ክልላቸው የሚመርጡትን ከተማ ለይተው እንዲያሳውቁና አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፣

### 7.2.2. የቁጠባ ሥርዓት

ሀ. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የሚያገለግል አመቺ አሰራር ለመዘርጋት በሚያስችለውና በሚዘጋጅ መንገድ ለእያንዳንዱ ማህበር ሂሳብ እንዲከፈት ያደረጋል፣

ለ. የመጀመሪያውን ቁጠባ በመረጡት የቤት አይነት መጠን ከ50 በመቶ እስከ 100 በመቶ በኢምባሲያቸው አማካኝነት ህጋዊነቱ እንዲረጋገጥ በማስደረግ በማህበሩ ስም እንዲልኩ ይደረጋል፤

ሐ. በእያንዳንዱ ሂሳብ መላክ ያልቻለ ማህበር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዚህ ስራ ያገለግላል ብሎ ወደ ተዘጋጀው አካውንት እንዲልክ በማድረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በተወካዮቻቸው አማካኝነት ዝርዝሩን በማየት ወደ እያንዳንዱ ማህበር አካውንት እንዲገባ ይደረጋል፣

መ. ቀሪውን የቁጠባ መጠን (50 በመቶ) በመመሪያው መሰረት ወደ እያንዳንዱ ማህበር የቁጠባ ሂሳብ እንዲገባ ይደረጋል፣

ሠ. አባላቱ ከዚህ በፊት በዲያስፖራ አካውንት ስም የተከፈተ ሂሳብ ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ቁጠባ ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፣

ረ. ቁጠባ የሚደረገው ለመመዝገብ የፈለጉትን የቤት አይነትና የቁጠባ መጠን ከውጭ ምንዛሪ ወደ ኢትዮጵያ ብር ተቀይሮ በማንኛውም ኢትዮጵያ በምትገበያይባቸው የውጭ ምንዛሪ (በዶላር ዩሮና ፓዉንድ ስተርሊንግ) ነው።

ሰ. በሀገር ውስጥ በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በብር መቆጠብ ይችላሉ፣

ሸ. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ምንዛሪ የተላከውን ገንዘብ ወደ ሀገር ውስጥ ገንዘብ በመቀየር የተከፈተው ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል፣

### 7.2.3. የመኖሪያ ቤቶች ስፋት፣ ጠቅላላ ዋጋ እና ቅድመ ቁጠባ

- ባለ 1+1 መኝታ ስፋቱ 60 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋው 210,000 ሲሆን ቅድሚያ ክፍያው ብር 105,000 በኢትዮጵያ ብር ነው።
- ባለ 2+1 መኝታ ስፋቱ 80 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋው 280,000 ሲሆን ቅድሚያ ክፍያው ብር 140,000 በኢትዮጵያ ብር ነው።
- ባለ 3+1 መኝታ ስፋቱ 110 ካ.ሜ፣ ጠቅላላ ዋጋው 385,000 ሲሆን ቅድሚያ ክፍያው ብር 192,500 በኢትዮጵያ ብር ነው።

- ከላይ የተጠቀሱት ዋጋዎች የማጠናቀቂያ ዋጋ የማያካትቱ ሲሆን የሚያገለግሉት ለምዝገባና ቁጠባ ለማድረግ እንጂ የቤቶቹ ትክክለኛ የማስተላለፊያ ዋጋ የሚወሰነው ግንባታው ተጠናቆ በወቅቱ በሚወጣው ዋጋ መሰረት ይሆናል፣
- የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 100% መቆጠብ የሚችሉትን በማበረታታት በመመሪያው መሰረት በመረጡት የመኖሪያ ቤት ዓይነት በማደራጀት ዝርዝሩ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲቀርብ ይደረጋል፣

## 7.2.4. ተግባርና ኃላፊነቶች

### 7.2.4.1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ሀ. በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊነት ለሚመዘገቡ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበራቱን በማደራጀት፣ የምዝገባና የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት የሚሳተፉ አካላትና ተቋማትን የተቀናጀና የተናበበ አሰራር እንዲከተሉ የሚያግዝ ማስፈጸሚያ ሰነድ በማዘጋጀት ስለ አፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ለ. ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመሆን ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ግንባታ የሚውሉ በቂ የመሬት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን አዘጋጅቶ የማቅረብ ወይም በማህበራቱ በራሳቸው ተዘጋጅተው የቀረቡትን ዲዛይኖችን የማጸደቅና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ በተቀናጀ አግባብና በጸደቀው የቤት አቅርቦት ስትራቴጂ መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

### 7.2.4.2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

#### 1) የሚሲዮኖች አጠቃላይ የስራ ድርሻ

ሀ) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ለተደራጁ ቤት ፈላጊዎች ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ በሚሲዮኑ እንዲሁም ለሚወክሉባቸው አገሮች/ከተሞች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፣

ለ) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም መመሪያው ላይ የተቀመጠውን የምዝገባ ቀናት፣ የምዝገባ ቦታና ተመዝጋዎች የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እንዲያሟሉ በግልጽ የማስገንዘብ ስራ መስራት፣

ሐ) ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች እንዲሞሉ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተላኩ ቅጾችን በበቂ ሁኔታ በማዘጋጀት ማስሞላት፣

መ) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም የተመዘገቡትን እንዲሁም የተሞሉ ቅጾችንና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን በጥንቃቄ በማደራጀት በዲፕሎማቲክ ፓውች

በወቅቱ ለውጭ ጉዳይ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲደርስ ማድረግ፣

ሠ) ስለ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን የተለያዩ ሰነዶች፣ ቅጾችና ውሎች በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣

ረ) ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች እንዲሁም ማብራሪያ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ካጋጠሙ በጊዜው ለዋናው መ/ቤት ማቅረብ፣

ሰ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ብቻ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

## 2) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ምዝገባ ፕሮግራም የሚሲዮኖች የስራ ድርሻ

ሀ) ምዝገባው የሚጸድቀው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኩል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በመመሪያው መሰረት ማከናወን፣

ለ) በመመሪያው መሰረት ነባርና አዲስ የተደራጁ ማህበራት እንዲሁም በአባሎቻቸው የተሞሉ ቅጾች ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች በዲፕሎማቲክ ፓውች እንዲደርስ ማድረግ፣

ሐ) በእያንዳንዱ ነባርም ሆነ አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተሞሉ የአባላት ቅጾች፣ የተደራጁበት የመተዳደሪያ ደንብ፣ የአመራር አባላትን የመረጡበት የተፈረመ ቃለ ጉባኤ፣ የፈለጉትን የቤት አይነት ዋጋ 50 በመቶ፣ ከአባላቱ የተሰበሰበ የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ፣ የተላከበትን ደረሰኝ ከሚሲዮኑ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር መላክ፣

መ) አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላት 24 እና ከዚያ በላይ አባላት ሆነው የሚተዋወቁ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ነባር ከሆኑ ከ16 ያላነሱ መሆኑን በማረጋጋጥ ሚሲዮኑ ሞዴል የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ እንዲሞሉት በቃለ ጉባዔም የተደገፈ አመራር አባላት መምረጥና ተፈራርሞ መላክ፣

ሠ) ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላት የሚገነቡት ቤት አይነት በኢንተርፕራይዝ ወይም ራሳቸው በመረጡት ስራ ተቋራጭ የሚገነባ መሆኑን ለይተው እንዲያቀርቡና በሚመርጡት ዓይነት በቅድሚያ የሚጠበቅባቸውን ዋጋ ከ50 በመቶ እስከ 100 በመቶ ገንዘብ መላካቸውን ማረጋገጥ፣

## 7.3. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጄኔራል የስራ ድርሻ

ሀ) ከሚሲዮኖች ጋር በቅርበት በመገናኘት ተፈላጊ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ቅጾች፣ የማህበራት መመስረቻ ቃለ ጉባዔ፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች ሰነዶችና ፎርሞች በወቅቱ ለሚሲዮኖች መላክ፤

ለ) ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር በወቅቱ ለሚሲዮኖች እንዲደርሱ ማድረግ፣

ሐ) ከሚሲዮኖች የሚላኩ የተሞሉ ቅጾችንና መረጃዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደትና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማድረስና ስለጉዳዩ ክትትል ማድረግ፣

መ) የመኖ/ህ/ስ/ማህበራትን የምዝገባ ዕውቅና የሚገልጽ ደብዳቤ ከአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ሲላክ ለሚሲዮኖች ማስተላለፍ፣

ሠ) ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚሲዮኖች በተላከው መረጃ መሰረት በባንኩ የተፈረመ የውል ሰነድ ኮፒ እንዲሁም የተዘጋጀ በተመዘገበው ስም የተከፈተ የተሟላ የቁጠባ ደብተር ተቀብሎ ለሚሲዮኖች መላክ፣

ረ. በውጭ የሚኖሩ ሆነው በምዝገባው ወቅት በአካል የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ /ማህበር አባላትን በተመለከተ ከአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ከፍቶ ምዝገባውን ያከናውናል፣

ሰ. ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመሆን ሂሳብ ከተከፈተ በኂላ ዝርዝሩን የአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ያስረክባል፣

ሸ. ከሚሲዮኖች፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት የሚደረጉ ግንኙነቶችን በተመለከተ መከታተልና መረጃ መያዝ፣

ቀ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከላካቸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ዝርዝር ውስጥ ዕውቅና ለማግኘት ችግር ያለባቸው ከሆኑ የማስተካከል ወይም ከባንክ ሂሳብ አከፋፈት ጋር የተያያዙ ችግሮችን የመፍታት ኃላፊነት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል፣

### 7.2.4.2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ሀ. በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች የሚያስፈልግ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ጋር በጋራ ይሰራል፤

ለ. ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውና በመመሪያው መሰረት የተደራጁ ማህበራትን በኢምባሲዎች አማካኝነት በማጣራትና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመላክ ቅድመ ምዝገባ በማድረግ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር በሚልከው ዝርዝር መሰረት በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ይደረጋል፤

7.2.4.3. **የአዲስ አበባ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት**

ሀ. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ለመመዝገብ የሚያስፈልጋቸውን የአደረጃጀት መመሪዎችንና ቅጾችን ያሳውቃል፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደአስፈላጊነቱ ውክልና በመስጠት እንዲደራጁና የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፍቱ ያደርጋል፣

ለ. በውጭ ለሚኖሩ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አማካኝነት ለመደራጀት የሚያስፈልጋቸውን ዝርዝር መመሪያና ሞዴል ቅጾች በማዘጋጀት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

ሐ. ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው በአዲስ አበባ ከተማ የቤት ፈላጊነት ምዝገባ ለመጠቀም በውጭ የተደራጁ (ካሉ) ነባርና አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ያደርጋል፣ የቤቱን ዋጋ ከ50 በመቶ እስከ 100 በመቶ ያሟሉና ሌሎች ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

መ. የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተላከለት ዝርዝር መመሪያ መሰረት ቁጠባ ያጠናቀቁ የህብረት ስራ ማህበራትን ቤት ለመስራት ለመረጡበት ክፍለ-ከተማ በመላክ በክፍለ-ከተማው የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ልማት የስራ ሂደት አማካኝነት የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

ሠ. የተመዘገቡና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ለከተማው አስተዳደር የመሬት ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል፣

7.2.5. **ልዩ ልዩ ጉዳዮች**

አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ስራ ማህበራት የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በሚደረግበት ወቅት ልዩ ትኩረት አድርገው የሚከታተሏቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ይሆናሉ፣

1) **የምዝገባ ጊዜ**

የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ጊዜ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ የሚጠናቀቅ ሆኖ በቦታ እርቀትና በመረጃ እጥረት ምክንያት በወቅቱ ያልደረሱ መረጃዎች ካሉ ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

2) **የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ**

ሀ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንቡና ለመኖሪያ ቤት ቁጠባ በዝግ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ ስለማንቀሳቀስ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በሚገቡት ውልና ሂሳቡን እንዲያንቀሳቅስ በተስማሙት ህጋዊ ተወካይ ወይም አመራሮች መሰረት ይሆናል፣

3) **የግንባታ ክትትልን በተመለከተ**

ሀ) በማህበር የተደራጁ አባላት የግንባታ ክትትልን በተመለከተ በውክልና ወይም የራሳቸው አማካሪ በመቅጠር ክትትል ሊያደርጉ ይችላሉ፣

ለ) በመንግስት ድጋፍ በቤቶች ልማት ኢንተርፕራዝ አማካኝነት ቤቱ እንዲገነባላቸው የሚፈልጉ ከሆነ መንግስት አማካሪ በመቅጠር የግንባታ ክትትል ሊያደርግ ይችላል፣

ሐ) ራሳቸው በመረጡት ወይም በሚቀጥሩት ስራ ተቋራጭ ግንባታ ለማከናወን ከፈለጉ የግንባታ ክትትሉ በራሳቸው ፍላጎት በሚቀጥሩት አማካሪ አማካኝነት ይሆናል፣

4) **ቤት ርክክብና ቅድሚያ አወሳሰን**

ሀ) ከዚህ በፊት በማህበር ተደራጅተው የነበሩ የዲያስፖራ ተጠቃሚዎች በድጋሚ በዚህ መመሪያ መስፈርቱን አሟልተው ከተመዘገቡ ከአዲስ ተመዝጋቢ ማህበራት ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፣

ለ) በማህበር የተደራጁ አባላት የቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል እና ከአማካሪ ጋር በገቡት ስምምነት የሚፈጸም ሲሆን ለእያንዳንዱ የማህበር አባል የቤት ርክክብ የሚፈጸመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አማካኝነት ይሆናል፣

5) **ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ**

ሀ) ተመዝጋቢ ማህበር በተመዘገበበት ፕሮግራም በፈቃደኝነት ከፕሮግራሙ ለመውጣት ከፈለገ ወይም የሚጠበቅበትን ቀሪ 50 በመቶ ክፍያ መክፈል ካልቻለ ከምዝገባው ተሰርዞ በቅድሚያ የከፈለው 50 በመቶ ክፍያ በኢትዮጵያ ብር እና በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት ወለዱ ታስቦ ይመለስለታል፣

ለ) ተመዝጋቢው ማህበር የምዝገባ መመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እንደሆነ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ በህግ ሊጠየቅ ይችላል፣

ሐ) ሆኖም ከማህበሩ አባላት ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት አባላት መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆነ በግል ተጠያቂ ሆነው ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚቀጥል ይሆናል፣

6) **ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ**

ሀ) ከመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነ ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማህበር የሚመለሰው ገንዘብ በወቅቱ የኢትዮጵያ ገንዘብ ሆኖ በቁጠባ ውሉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚያገኘውን የወለድ ጥቅም በመጨመር ነው፡፡

7) **ክልከላ**

ሀ) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 01/2005 በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚመለከት ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ መመዝግብም ሆነ እንዲመዘገብ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ለ) በመመሪያው የተቀመጡ ክልከላዎች በሙሉ በዚህ ማስፈጸሚያ ሰነድ ተፈጻሚነት አላቸው፣

8) **ቅጣት**

የነባርና አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 01 /2005 የተቀመጡትን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ፣ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ እንደሆነ አግባብ ባለው በወንጀልም ሆነ በፍትሕ ብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

8. **ማስፈጸሚያ ሰነዱን ስለማሻሻል**

ይህን ማስፈጸሚያ ሰነድ ማሻሻል ሲያስፈልግ የጋራ አስፈጻሚ አካላት ሊያሻሽሉት ይችላል፡፡

9. **ማስፈጸሚያ ሰነዱን የሚጸናበት ገዜ**

ይህ ማስፈጸሚያ ሰነድ በ------ ተፈርሞ ከወጣበት ከ------ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፣

--------------- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

--------------- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

-------------- የአ/አ/ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

-------------- የፌዴራል ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ

**ቅጽ 007**

**አባሪ አንድ ፡- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በ40/60 ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ የቤት ፍላጎት መግለጫ ቅጽ**

1. የአመልካች ሁኔታ፣
   1.1. ስም -------------------- የአባት ስም ------------------የአያት ስም --------------------
   ፆታ -------ዕድሜ---------ብሔር-----------------ዜግነት------------የፓስፖርት ቁጥር-------------------
   የትዉልድ እትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ቁጥር-----------
   1.2 የአመልካች እናት ስም ----------------------- የእናት አባት ስም -----------------------------
   የእናት አያት ስም ------------------------------------
   1.3 የመኖሪያ አድራሻ
   - አገር------------------------------------ከተማ------------------------------------
   - ፖ.ሳ.ቁ.--------------------------------- ፋክስ ቁጥር---------------------------
   - ስልክ ቁጥር-------------------------------ኢሜል -----------------------------

   1.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐
   1.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም---------------የአባት ስም---------------- የአያት ስም -------------------
2. የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት
   ባለ 1 መኝታ ☐ ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐

3. የገቢ ሁኔታ
   3.1. የአመልካች ወርሃዊ የገቢ መጠን --------------------------- ምንጭ -------------------
   3.2. የትዳር ጓደኛ የገቢ መጠን ----------------------- ምንጭ -------------------------------
   3.3. ጠቅላላ የገቢ መጠን በአኃዝ ------------ /በፊደል-----------------------------------/
4. የተወካይ መረጃ፤(ካለ)
   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት---------------------------------------------------------------

   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
   - ክልል---------------------------ከተማ--------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ------------------------------ወረዳ ---------------------------
   - ቀበሌ ---------------------------የቤት ቁጥር ----------------------------
   - የቤት ስልክ ቁጥር ------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ----------------------
5. ለምዝገባ የሚያስፈልግ የቁጠባ መጠን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ
   5.1 በቅድሚያ በልዩ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጠው ዝቅተኛ የቁጠባ መጠን ብር በአኃዝ ------------------

   /በፊደል-----------------------------------------------------------------------------------------------/

   5.2 የዝግ ሂሳብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ----------------------------------- ቅርንጫፍ ----------------------
6. የቁጠባ ሂሳብ የሚከፍትበትና የቤቱን ዋጋ ክፍያ የሚፈጸምበት አማራጭ መንገድ፡-

6.1. ሙሉ ክፍያ (100%) በአንድ ጊዜ ☐

6.2 40% በአንድ ጊዜና ቀሪውን 60% በውሉ መሰረት በየወሩ በተከታታይ የሚከፈል ☐

6.3. የየወሩን ቁጠባ መጠን በየወሩና ቅድሚያ ክፍያ 40 በመቶ በአምስት ዓመት ሆኖ ቀሪውን 60% የቤት ዋጋ ክፍያ በህጉ ወይም በውሉ መሰረት በየወሩ በተከታታይ የሚከፈል ☐

7. እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

7.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

7.2 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በመንግስት በተዘረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

7.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ዋጋ ወርሃዊ/ የመጀመሪያ ቁጠባ በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ መሆኑን፣

7.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

7.5 እኔም ሆነ የትዳር ጓደኛዬ የምንኖረው በመንግስት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል የገዛሁትን ቤት በተረከብኩ በ30 ቀን ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኔን፣

7.6. በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረክብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

7.7 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

7.8 ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም------------------------------------

ፊርማ -------------------------------

ቀን --------------------------------

ቅጽ 005

## አባሪ ሁለት ፡- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵውንና ትውልደ ኢትዮጵውያንን በመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ

ፎቶ

2. የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ-------------------------------------------------------------
   የመኖሪያ ቤት ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ
3. የአመልካች ሁኔታ፣
   2.1. ስም --------------- የአባት ስም -----------------የአያት ስም ---------------------
   ፆታ -------- ዕድሜ---------- ብሔር-------------- ዜግነት--------------- የፓስፖርት ቁጥር------------
   የትዉልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ቁጥር-----------

   1.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------ የእናት አባት ስም ------------------------------
   የእናት አያት ስም-------------------------------------

   2.3 የመኖሪያ አድራሻ
   - 2.3.1 አገር-------------------------------------
   - 2.3.2 ከተማ------------------------------------

   2.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

   4.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም ----------------- የአባት ስም ------------------ የአያት ስም---------------
5 የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት
   3.1 ቪላ ከሆነ ፤
   ባለ 1 መኝታ ☐ ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ሌላ ------------------------

   3.2 የጋራ ህንጻ (ፎቅ) ከሆነ፡

   ባላ 1 መኝታ ☐ ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ሌላ--------------------------

   3.1 በራሳቸው ዲዛይን ለሚገነቡ የሚፈልጉት የቦታ ስፋት -------------- ካ.ሜ

6 የተወካይ መረጃ፤
   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት----------------------------------------------------------------

   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
   - ክልል---------------------------ከተማ--------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ-------------------------------ወረዳ ----------------------------
   - ቀበሌ ---------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------
   - የቤት ስልክ ቁጥር -------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር -----------------------
5 እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች
   5.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

5.2 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በቤት ልማት ፕሮግራም ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ ዋጋ 50 በመቶ በምዝገባ ወቅትና ቀሪውን 50 በመቶ ለማህበሩ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ የማስቀምጥ መሆኑን፣

5.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.5 እኔም ሆነ የትዳር ጓደኛዬ የምንኖረው በመንግስት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ቤቱን በተረከብኩ በ 30 ቀን ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.6 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረክብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

5.7 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

5.8 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያማላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-----------------------------------

ፊርማ -------------------------------

ቀን ---------------------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህ/ስ/ማህበሩ አባል ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው